# በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የሚቋቋሙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

## ቁጥር 854/2014

# በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የሚቋቋሙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 854/2014

የዱር እንስሳት ሃብት ባልተቀናጀና አግባብነት በሌለው አጠቃቀም ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነና ለአደጋ ተጋላጭነቱ እየጨመረ በመምጣቱ፤

በዱር እንስሳትና በዱር እንስሳት ውጤት ላይ የሚደረገው ንግድ የዱር እንስሳቱን አደጋ ላይ የማይጥልና ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዱር እንስሳት ኢ-ፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልት አማካይነት ከዱር እንስሳት ሃብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማጎልበት ለሀገሪቱ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በሚቋቋሙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ ወጥነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ቀደም ሲል ለወጡት የዱር እንስሳት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 እና የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ማስፈጸሚያ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 17 (2) በተደነገገው መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚቋቋሙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 854/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) **“አዋጅ”** ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፡፡
2) **“ደንብ”** ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ነው፡፡
3) በአዋጁ እና በደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
4) **“የዱር እንስሳት ጥብቃ ቦታ”** ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የተከለለ ሥፍራ ሲሆን፤ ብሔራዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፓርክን፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችን፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ክልሎችን እና የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ይጨምራል፡፡
5) **“አገልግሎት ሰጪ ተቋም”** ማለት በዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎች ውስጥ የሚቋቋም ሎጆችንና ካምፕ ነው፡፡
6) **“ባለሃብት”** ማለት በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በማቋቋም ለቱሪስት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፡፡
7) **“ፈቃድ”** በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለማቋቋም ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
8) **“የፕሮጀክት ንድፍ”** ማለት በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለማቋቋም የተቀረጸና የሥራውን ዝርዝር ተግባራትና መርሃ-ግብር ያካተተ ሰነድ ነው፡፡
9) **“ሚኒስቴር”** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው
10) **“ባለስልጣን”** ማለት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡
11) **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
12) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>**የመመሪያው ዓላማ**</u>

1. በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ ቱሪዝም በላቀ መልኩ እንዲስፋፋና ኢንቨስትመንት እንዲበረታታ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ንዑስ ዘርፉ ለአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ማድረግ፤
2. የዱር እንስሳት አቀፍ ቱሪዝም ዘለቄታዊነትን በሚመለከት ተገቢውን ክትትል ማድረግና የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤
3. የዱር እንስሳት አቀፍ ቱሪዝም እንቅስቃሴን ለማሳለጥ፣ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠትና ወጥነት ያለውን አሰራር መዘርጋት፤
4. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ የሚሰሩት መሰረተ ልማቶች የሚያደርሱትን አሉታዊ ተጽእኖ ለመቋቋምና የአሉታዊ ተጽእኖ ማቃለያ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

4. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ መመሪያ በፌዴራል መንግስት በሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎች መስፈርት

5. <u>**ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ተግባራት**</u>

1) በዱር እንስሳት ጥብቃ ቦታዎች ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት የአገልግሎት ሰጪ ተቋም ሆነ የመሠረተ ልማት ግንባታ ለማካሄድ በቅድሚያ የባለስልጣኑን የፅሁፍ ፍቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡
2) ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተቋቋሙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፀንተው ይቆያሉ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀው ሆኖ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ አስፈላጊውን የመስፈርት ቅድመ ሁኔታ የማሟላት ግዴታ አለባቸው፡፡

## 6. ስለጥያቄ አቀራረብ

1. አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለማቋቋም ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማመልከቻና አስፈላጊ መረጃዎችን በማሟላት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ማመልከቻው፤ የፕሮጀክቱን አጭር ማብራሪያ፣ የካፒታሉን መጠን፤ ልማቱን ለማከናወን የታቀደበት ቦታና ጊዜ፤ ፕሮጀክቱ የሚኖረው ምጣኔ ሃብታዊ ፋይዳና ለኅብረተሰቡ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ማካተት ይኖርበታል፡፡
3. ባለሥልጣኑ የቀረበውን ማመልከቻ ገምግሞ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡
4. አመልካቹ ያቀረበው ጥያቄ ጉድለት ያለበት ሆኖ ከተገኘ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አሟልቶ እንዲያቀርብ ይመለስለታል፡፡
5. ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መረጃውን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡

## 7. ስለቦታ መረጣ

አገልግሎት ሰጪ ተቋምን ለማልማት የሚመረጠው ቦታ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

1. በዱር እንስሳት ጥበቃ ለዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው የተዘጋጀና ወደፊት ከሚዘጋጅላቸው ሥርአተ-አያያዝ ዕቅድ /የማኔጅመንት ፕላን/ ጋር የተጣጣመ መሆኑ፤
2. የአካባቢ ተፅዕኖ ቅኝት ለጥበቃ ቦታው ዋና ዓላማ ቅድሚያ የሰጠና ሚዛናዊነትን ያለው መሆኑ፤

3. በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ አነስተኛ መሆኑ፤
4. ልዩ ትኩረት በሚሠጣቸው የዕፅዋትና እንስሳት ሀብቶች በተለይም በአገሪቷ ብቻ በሚገኙ፣ ዝርያቸው ሊጠፋ በተቃረበ፣ ቁጥራቸው በተመናመነ፣ ወይም ለአደጋ በተጋለጡ እንስሳት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የማያስከትል መሆኑ፤
5. የዱር እንስሳቱ የሚንቀሣቀሱበትን አካባቢ፣ የመራቢያ ቦታቸውን፣ በደረቅ ወራት የሚጠለሉበትን አካባቢ፣ የመመገቢያና የውሃ መጠጫ፣ ቁልፍ የመኖሪያ አካባቢያቸውን የማይረብሽ፣ የማይበክል እና የማያጠፋ መሆኑ፤
6. በጥበቃ ቦታዎች በሚገኝ ማንኛውም የውሃ ሃብት ምንጭና መገኛ መጠንም ሆነ ጥራት ላይ በማናቸውም ሁኔታ አሉታዊ ተፅእኖ የማያሳድር፣ የማይበክል ወይም የማይመርዝ መሆኑ፤
7. በዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታ ወሳኝ ጠቀሜታ ባላቸው አትኩሮት በሚሰጣቸው ቦታዎች፣ ገጽታዎች፣ የመሬት አቀማመጦችና የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ አፍራሽ ተጽዕኖ የማያስከትል መሆኑ፤
8. ቱሪስቶች በዋናነት በሚጎበኙዋቸው መስህቦችና ለእይታ በሚጠቀሙባቸው አካባቢዎች ላይ አለመሆኑ፤
9. በዕፅዋት ወይም በመሬት ገጽታ በተከለለ፣ በአካባቢው ጎልቶ በማይታበትና ከመሬት ገጽታው፣ ከእጽዋትና መልክአ ምድሩ ጋር በቀላሉ ሊዋሃድና ህብር ሊፈጥር በሚችልበት ቦታ ላይ መሆኑ፤
10. በቅሪተ አካል መገኛዎች፣ በታሪካዊ ቦታዎች ወይም ባህላዊ፣ ማህበራዊና ሀይማኖታዊ አትኩሮት በሚሰጣቸው ቦታዎች ላይ አፍራሽ ተጽእኖ የማይፈጥር መሆኑ፤
11. ለዋናና የውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ ለህንፃ ግንባታና ለቆሻሻ ማስወገጃ አመቺነት ያለው ቦታ መሆኑ፡፡

8. <u>የቦታ አሠጣጥ</u>

1. አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የሚለማበት ቦታ መረጣ በባለሥልጣኑ ይከናወናል፡፡

2. የሥርዓተ አያያዝ (ማኔጅመንት ፕላን) ካላቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለአልሚዎች የሚሰጠው ቦታ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲውል ተብሎ ከተለየው ቦታ ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡
3. የቦታ መረጣ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ መቅረብና መፅደቅ ይኖርበታል፡፡
4. የቦታ መረጣው ከተከናወነ በኋላ ባለሀብቱ በአንቀጽ 9 የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

## 9. <u>የፈቃድ መስፈርቶች</u>

በጥብቃ ቦታዎች ውስጥ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለማቋቋም የሚሰጥን ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1) የንግድ ምዝገባና የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣
2) ከጠቅላላ የጥበቃ ቦታው ሥርአተ-አያያዝ ዕቅድ ወይም የልማት ዕንሠ ሀሣብ ጋር የተጣጣመና የተቀመጡትን ገደቦች ግምት ውስጥ ያስገባ ዝርዝር የተግባር ዕቅድ እንዲሁም የቦታውን ካርታና የግንባታውን ዲዛይን፣
3) ልማቱ በተፈጥሮ ሀብትና በዱር እንስሳት ላይ የሚያደርሰውን የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ በገለልተኛና ህጋዊ አካል የተጠና ሪፖርት፤
4) የልማቱ ግንባታ ወጪ ሠላሳ በመቶ /30%/ ስለመኖሩ ሕጋዊ የሆነ ማስረጃ፤

## 10. <u>የተግባር ዕቅድ /ፕሮጀክት ንድፍ/ ይዘት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ለማቋቋም የሚቀርበው የተግባር ዕቅድ የሚከተሉትን ይዘቶች ማሟላት ይኖርበታል፤

1. የፕሮጀክቱ አጭር መግለጫና ልማቱ በአካባቢው ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ሪፖርት፤
2. የተመረጠውን ቦታ፣ ከፀደቀው የፓርኩ ሥርዓተ አያያዝ፣ የጥበቃ ቀጠና አመዳደብና ስለአጠቃቀሙ ከተቀመጡት ገደቦች ጋር የሚስማማ ስለመሆኑ አሳማኝ ምክንያቶችን በግልፅ ማመላከት፤
3. የልማቱን ዓይነት (የቱሪስት ማረፊያ ቦታ ፣ሪዞርት ቋሚ ወይም ተንቀሳቃሽ ካምፕ በውስጡ የሚኖረውን፡-

ሀ. የምግብ አዳራሽ፣የባህል ሙዚቃ ማሣያ፣ መጸዳጀ ቤት፣ ሱቅ፣የልብስ ንጽሕና መስጫ፤

ለ. የክፍሎቹን፤ የአልጋዎቹን፣ የውጭ ማረፊያዎችን ብዛትና ደረጃ፣ ማመላከት፤

4. ለቱሪስቶች ስለሚቀርቡ የአገልግሎት ዓይነቶች በተለይም ለእንግዶች የሚደረገው አቀባበል፣ ስለመረጃ አሠጣጥ፣ ትምህርታዊ ኘሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች፣ መዝናኛ ፕሮግራሞችን እንዲሁም የመጓጓዣ ዘዴዎችን፣ መግለፅ፤
5. የሚቀጠሩ ሠራተኞች ብዛት፣ ከየት እንደሚቀጠሩና የአቀጣጠር ሁኔታ፣
6. የአካባቢው ህብረተሰብ ከፕሮጀክቱ የሚያገኘውን ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅም በአካባቢው የተመረቱ የተለያዩ ውጤቶችን ከመሸጥ፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች ከማግኘት፣ የሥራ እድል ከመፍጠር አንፃር እና የመሣሠሉትን በግልፅ ማመላከት፤
7. አጠቃላይ የልማቱ ኪነ-ህንጻዊ መዋቅር ከሚሰጠው አገልግሎት፣ ከሚሠራበት የግንባታ ቁሳቁስ፤ ከህንፃው የውጭ ቀለም እና ከተፈጥሮ አካባቢው ጋር የሚኖረው ውህደትና ህብር አስመልክቶ የተሟላ መግለጫ መያዝ፤
8. የውሃ መገኛ ምንጩን፣ አጠቃቀሙን፣ መጠኑን፣ የማከፋፈያና የማደሻ መንገዶቹን እንዲሁም የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎቹን መግለፅ፤
9. የኃይል ምንጩን ዓይነት፣ የሚተከልበትን ቦታ፣ የድምጽ መቀነሻ ስልቱን፣ የኃይል ማሠራጫ ቴክኒኩን የነዳጅና ኬሚካል ማከማቻውን፣ ሌሎች አገልግሎቶችንና ተዛማጅ ምቹ ሁኔታዎችን በግልጽ መጠቀስ፤
10. ለመሥራት የሚታሰቡ መንገዶች፣ ውስጥ ለውስጥ ፍሳሽ መተላለፊያ ተከፍቶ የሚታይባቸው ቦታዎች፣ ድልድዮች፣ ወይም ሌሎች ፍሳሽ ከመሬት በላይ የሚተላለፍባቸው መንገዶችና የመቆጣጠሪያ ስልቶች እንዲሁም መሠረተ ልማቶች ለአይን ማራኪ እንዲሆኑ የሚወሰዱ እርምጃዎችን መግለፅ፤
11. በየዕለቱ በመንገድ ላይ ሊኖር የሚችለው የትራፊክ እንቅስቃሴ ብዛት፣ ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተግባራት የሚገለገሉባቸው ተሽከርካሪዎች ብዛትና ዓይነት፣ የስምሪት ኘሮግራምና ጊዜ እንዲሁም የማቆሚያ ሥፍራን መግለፅ፤

12. የልማት አካባቢውን ለማስዋብ በሚደረገው እንቅስቃሴ በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉትን የአፈርና የአገር በቀል እጽዋት ዓይነቶች ሳይንሳዊ ስም፣ በዝርዝር መያዝ፤
13. የግንባታ አወቃቀሮቹ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆኑን፤
14. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው ከልማቱ ሊያገኘው ስለሚችለው ጥቅም በዝርዝር ማሳየት፤
15. በግንባታው ዝርዝር ገለጻ ውስጥ፣

    ሀ. ግንባታው የሚፈጀው ጊዜ፣ ግንባታው በየምዕራፉ የሚቆይበት ጊዜ እና የየቀኑን የግንባታ የሥራ ሰዓት፣

    ለ. ለግንባታው የሚያገለግሉ ዕቃዎች ዝርዝር፣ የአቅርቦት ሁኔታቸውን ጨምሮ የግንባታ መሣሪያዎች ምንጭ፣ የጭነት መኪናዎች ዓይነትና ብዛት፣ የጭነት መኪናዎቹ በብዛት የሚንቀሳቀሱበት ሰዓት፣ ጊዜያዊ የዕቃዎች ማከማቻ ቦታ፤

    ሐ. ለግንባታው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ብዛት፣ ጊዜያዊ የሠራተኞች ቢሮ ቦታና ስፋት፣ የምግብ አቅርቦት፣ የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ዕርዳታ አገልግሎቶች፣

    ረ. የውሃና የኃይል ምንጭ፤ የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ዘዴ፣

    ሸ. በግንባታ ወቅት በጥቅም ላይ እንዲውሉ በጥበቃ ቦታው ውስጥ የሚሠሩ ጊዜያዊ መንገዶችን ወደነበሩበት ተፈጥሮአዊ ሁኔታ የሚመለሱበት ዕቅድ፤

    ቀ. በግንባታ ወቅት በአካባቢው ላይ ሊደርስ የሚችለውን አፍራሽ ተጽእኖ ለማስወገድና ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ ተጽእኖ የደረሰበትን አካባቢ እንዲያገግም የሚያስችል ዕቅድ፤

መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

16. የፕሮጀክቱ ምጣኔ ሀብታዊ አዋጭነት መገለጫ ላይ፡-

    ሀ. ልማቱ በገበያ ላይ ያለው ተፈላጊነት፤

    ለ. የጥቅምና ጉዳት ንጽጽር ትንተና፤

ሐ. አልሚውና ባለሥልጣኑ ከፕሮጀክቱ ሊያገኙ የሚችሉት ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም፤

መ. አልሚው ወጪውን ለመመለስ የሚፈጅበት ጊዜ

መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

## 11. ስለቦታው ካርታ

1. የግንባታ ቦታውንና የልማት ዕቅዱን የያዘ ካርታና ዲዛይን የሚዘጋጅ ሆኖ፤ ካርታው የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡
   - ሀ. የቦታውን መልክአምድራዊ የተፈጥሮ ገጽታዎች፣
   - ለ. መሠረተ ልማትን ከመዘርጋት አኳያ ያሉትን ምቹ ሁኔታዎች፣
   - ሐ ሊሠሩ የታሠቡና የልማቱ አጋዥ የሆኑ ዋና ዋና መንገዶች፣ መኪና ማቆሚያ ሥፍራዎች፣ የውስጥ ለውስጥ መተላለፊያዎች፣ ድልድዮችና ሌሎች የልማት አውታሮች እንዲሁም በኤ 0 ወይም ኤ 1 ወረቀት ላይ የሠፈረ የቦታው ፕላን፣
   - መ. የፕላኑን ዲዛይን፣ ኪነ-ሕንጻውን የሚሠራው ድርጅት ሙሉ አድራሻ እና በእያንዳንዱ የስዕል ወረቀት ላይ የዋና ዋና ኪነ-ሕንፃ ባለሙያዎች ስምና ፊርማ፡፡
2. በፕላኑ ላይ ሊካተቱ የሚገባቸው ሥዕላዊ መግለጫዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡
   - ሀ. ኪነ-ሕንፃዊ ስዕሎች፤
   - ለ. የህንጻው ማረፊያ ፕላን፣
   - ሐ. የሁሉንም ህንጻዎች እያንዳንዱን የውስጥ ክፍሎችና ዋና ዋና አገልግሎታቸውን ከፋፍለው በስኬል ለይተው የሚያሳዩ ንድፎች፣
   - መ. በረንዳዎችን ወይም ከየደረጃው እስከ ሕንፃው ጫፍ የሚወስዱ መተላለፊያዎችን የሚያሳይ ንድፍ፤
   - ሠ. የመገናኛ መንገዶችን የሚያሳይ ንድፍ፤
   - ረ. ሕንጻው ሲጠናቀቅ የሚኖረውን የውጭና የውስጥ ገጽታ የሚያሳይ ንድፍ፤

ሰ. የዋናውን ሕንፃ /ሎጅ/ና የተያያዙ ግንባታዎችን የሚያሳይ ባለሦስት ጎን ኪነ-ሕንጻዊ ሞዴል፤

ሸ. የሥራው የአማካሪዎች ዝርዝር መረጃ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ተግባርና ኃላፊነት

12. <u>የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ደረጃውን የጠበቀ ውል በማዘጋጀት ፈቃድ ከተሰጣቸው አልሚ ባለሃብቶች ጋር ይፈራረማል፡፡
2. በጥብቅ ቦታዎች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ያሏቸውን የልማት እንቅስቃሴዎች ለማካሄድ የሚያቀርቧቸው የፕሮጀክት ንድፎች፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤን ስጋት ላይ የማይጥሉና በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎቹ የማኔጅመንት ዕቅድ መሠረት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
3. ባለሃብቱ ለሚያከናውነው የልማት ሥራ የሚውል በካርታ ላይ ተለይቶ የተመለከተ ቦታ ይሠጣል፤
4. ባለሃብቱ ለሚያከናውነው የልማት ሥራ የሚውል በካርታ ላይ ተለይቶ ለተመለከተው ቦታ ለኢንቨስትመንት ተግባር በሚውል የገጠር መሬት በፌዴራል የገጠር መሬት የኪራይ ተመን መሠረት ያስከፍላል፡፡
5. ባለሃብቱ ዓመታዊ የመንግሥት ግብር መክፈሉን፣ ፈቃዱ ወቅቱን ጠብቆ መታደሱንና ልማቱ ለአካባቢው ሕብረተሰብ የሚሰጠውን ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅም ያረጋግጣል፤
6. በተፈቀደው ቦታ ላይ የሚከናወንን ማንኛውንም የግንባታ ሥራ በተፈቀደለት መሥፈርት፣ ቦታና ፕላን መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፡ ይገመግማል የማስተካከያ ርምጃም ይወስዳል፤

7. ባለሃብቱ በፕሮጀክት ንድፉ ላይ ከተመለከቱት ክንዋኔዎች ጋር በተያያዘው የውሃና የመንገድ አገልግሎቶችን መጠቀም እንዲችል ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፤
8. ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሃብቶች በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶችና በውል በገቡት ግዴታ መሠረት እየሰሩ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
9. ግዴታቸውን በማይወጡ ባለሃብቶች ላይ አግባብነት ባለው ህግ መሠረት ርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

## 13. <u>የባለሀብቶች ተግባርና ኃላፊነት</u>

ማንኛውም ባለሀብት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. በዚህ መመሪያ፤ በባለስልጣኑ በፀደቀው የፕሮጀክት ንድፍ፣ በገባው ውልና አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት ልማቱን የማከናወን፤
2. በተሰጠው ቦታ ላይ ሊሠሩ የታቀዱ ሎጆችና ሌሎች የልማት አውታሮችን ከባለሥልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት ብቻ የመገንባት፤
3. በባለስልጣኑ ከተሰጠው ፈቃድ ውጪ ማናቸውንም ዓይነት የማሻሻያ ለውጦችን ያለማከናወን፤
4. ለዱር እንስሳቱና ለተፈጥሮ ሃብቱ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ የማድረግ፤
5. የዱር እንስሳቱ በጎብኚዎች ወይም በሠራተኞች የሚረበሹበት ሁኔታ እንዳይኖር አስፈላጊውን ጥንቃቄ የማድረግ፤
6. የመሠረተ ልማት ሥራው በጥበቃ ቦታው በሚገኙ የውሃ ሃብት ምንጮች መጠን፣ ጥራትና ደረጃ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር፣ የሚበክል ወይም የሚመርዝ እንዳይሆን አስፈላጊውን ሁሉ የማድረግ፤
7. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ መገልገያ መሣሪያዎችን፣ አሟልቶ በማቅረብ የተሟላ አገልግሎት የመስጠት፤
8. በጥበቃው ቦታ ለሚገኙ የመሠረተ ልማት አውታሮች ጥገናና ዕድሳት የማድረግ፤

9. ልማቱ በአካባቢው ሕብረተሰብ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ዕሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳይፈጥር አስፈላጊውን ጥንቃቄ የማድረግ፤
10. ከጠቅላላ ሠራተኛው ሁለት ሦስተኛው /67%/ የሚሆኑት ተቀጣሪዎች ከአካባቢው ማህበረሰብ እንዲሆኑ የማድረግ፤
11. በተፈቀደው ቦታ ላይ በስድስት ወር ውስጥ ግንባታውን መጀመርና በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ የማጠናቀቅ፤

## ክፍል አራት
## ፈቃድ ስለማደስና መሰረዝ

### 14. <u>ፈቃድ ስለማደስ</u>

ማንኛውም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ፍቃዱን በየዓመቱ ማደስ አለበት፡፡

### 15. <u>ፈቃድ ስለመሠረዝ</u>

1. ፈቃድ ሊያሠርዙ የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው
   ሀ. ፈቃዱን የወሰደው አካል በራሱ ፍላጎት ፈቃዱን ሲመልስ
   ለ. አገልግሎት ሰጪው ተቋም ከተቋቋመበት ዓላማ ውጭ እየሠራ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣
   ሐ. የዱር እንስሳቱንና የተፈጥሮ ሀብቶቹን ለአደጋ የሚያጋልጥ አሠራር መኖሩ ሲረጋገጥ፣
   መ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13(11) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ስራውን አለመጀመሩ ወይም አለመጠናቀቁ ሲረጋገጥ፣
   ሠ. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13 የተቀመጡት ተግባርና ኃላፊነቶች አለመተግበራቸው ሲረጋገጥ፤

ረ. በዚህ መመሪያም ሆነ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡ አለመወጣቱ ሲረጋገጥ፡፡

2. ፈቃድ ከመሠረዙ በፊት የአገልግሎት ሰጪ ተቋሙን ላቋቋመው አካል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና የሦስት ወር የማስተካከያ ጊዜ ይሰጠዋል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ሁኔታዎች የማይስተካከሉ ከሆነ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የአሰራር ሥርዓቶች ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 18. <u>ቅሬታዎችን ስለማስተናገድ</u>

1. በፈቃድ አሠጣጥም ሆነ መሠረዝ ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በባለሥልጣኑ መልስ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. ሚኒስቴሩ የቀረበለትን ቅሬታ ተመልክቶ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅረቢው ምላሹን ይሰጣል፡፡
4. ሚኒስቴሩ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

### 19. <u>ቅጣት</u>

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

### 20. <u>የስራ ማንዋል ስለማውጣት</u>

ባለስልጣኑ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም ዝርዝር የሆነ የስራ ማንዋል ያወጣል፡፡

**21. <u>ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች</u>**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በመመሪያው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**22. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**23. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ የካቲት 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አይሻ መሐመድ ሙሳ (ኢንጅነር)
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
ሚኒስትር